# ወያኔ ቆርጦ መቀጠልም ተሳናት !

## የአቶ አንዳርጋቸው ቃልና የወያኔ ፕሮፓጋንዳ

ሰሞኑን በወያኔ መንግስት የፖሊስ ፕሮግራም የቀረበው “አቶ አንዳርጋቸው ለመንግስት ጠቃሚ መረጃ ሰጡ” የሚለው ዜና ኢትዮጵያዊውን ሁሉ እያነጋገረ ያለ ጉዳይ ነው። የዜናው አነጋጋሪነት የሚነሳው ለዜናው አብይ ግብአት እንዲሆን፤ በወጉም ሳይታሰብበት ተለጣጥፎ የቀረበው የቪዲዮ ክሊፕ የዜናውን ጩኸት አለማስተጋባቱ ነው ።

በመጀመሪያ የምናነሳው ጥያቄ የወያኔ ባለስልጣናት ይህንን በተራ ግለሰብ እንኳ ቢቀርብ የሚያሳፍር ደካማ የማስመሰል ስራ በመንግስት ደረጃ ለማቅረብ ያስገደዳቸው ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ይመስለኛል።

ለዚህ ደግሞ የተለያዩ መላምቶችን መሰንዘር እንችላለን። መላምቶቹን ወደ ኋላ እንመለሰባቸዋለን። አሁን ለዜናው ግብአት ሆኖ በተለጣጠፈው ክሊፕ ውስጥ ምን አለ? አቶ አንዳርጋቸው ምን ተናገሩ? የቪዲዮው ምስላዊ ይዘትስ ምን ይመስላል? ወደሚሉት ተከታታይና ተወራራሽ ጥያቄዎች እናምራ።

### አቶ አንዳርጋቸው ምን ተናገሩ?

አቶ አንዳርጋቸው በቪዲዮው ላይ የተናገሯቸውን ነገሮች ፍሬ ሃሳብ ብቻ አጠር አጠር አድርጌ ላቅርብ።

- ፓስ ዎርድ ሲሰጡ ይደመጣል።
- ግንቦት ሰባትን በአይቲ የሚያግዙ ጥቂት ግለሰቦችን ስም ይጠሩና ሌሎችም በርካቶች እንዳሉ ይገልጻሉ።
- ማንነታቸውን በውል የማያውቋቸው ሶስት ሰዎች ለሚሽን መላካቸውንና ስለዋልድባ ሰዎች ይናገራሉ።
- ብዙ ስራ ስሰራ የነበርኩት እኔ ነኝ። እኔን ተክቶ ሊሰራ የሚችል ሰው እገሌ ብዬ መናገር ይከብደኛል ሲሉ ይደመጣሉ።
- በመጨረሻም፤ እንዲህ ነው፤ እንዲህ ነው ብሎ ማለት አይገባም ሰዎች መጨነቅ የለባቸውም እኔ ደህና ነኝ ይሉና ከሆነ ሰው ጋር ተጨባብጠው ይለያያሉ።
- ከ 55-70 ሰከንድ ድረስ አለፍ አለፍ ብሎ የስቃይ ደምጽ “ጩኸት” ይደመጣል።

አቶ አንዳርጋቸው የተናገሯቸውን ነገሮችን በተናጥል እንመልከት።

- **ፓስ ወርድ መስጠታቸው፡፤**

አቶ አንዳርጋቸው በተያዙበት ቅስበት እጃቸው ላይ የተያዘው ነገር ሁሉ በወያኔ እጅ ይገባል። ይህ ማለት ደግሞ አቶ አንዳርጋቸው ፓስ ወርድ ሰጡም አልሰጡም በ20 ደቂቃ ውስጥ ክራክ አድርገው ኮምፒውተሩ ውስጥ ያለውን መረጃ መግኘት ይችላሉ ማለት ነው። ይህ እየታወቀ ፓስ ወርድ መስጠታቸው እንደ ግዙፍ መረጃ በዜና ላይ መቅረቡ ራሱ ዜናውን ለማጮኽ ካልሆነ ውሃ የሚቋጥር ጉዳይ አይደለም።በርግጥ አቶ አንዳርጋቸው ላፕ ቶፑ እጃቸው ላይ ባይኖርና ወደ ተቀመጠበት ሌላ ቦታ መርተው ያሲያዙት ቢሆን ኖሮ በመጠኑም ዜናውን ዜና ዜና ባሸተተው ነበር።

- **ግንቦት ሰባትን በአይቲ የሚያግዙ ጥቂት ግለሰቦች ስም ይጠሩና ሌሎችም በርካቶች እንዳሉ ይገልጻሉ።**

አቶ አንዳርጋቸው ግንቦት ሰባትን በአይቲ ሙያቸው ይረዳሉ ብለው ስማቸውን የጠሯቸው ሰዎች የወያኔ ባለስልጣናት ቀደም ብለው በግንቦት ሰባት አባልነታቸው የሚያውቋቸው ናቸው። ማወቅ ብቻም ሳይሆን የስለላ ሶፍትዌር ሲልኩባቸው የነበሩ መሆናቸውን ልብ ይሏል። ያማለት ደግሞ እዚህም ጋ አዲስ መረጃ አልሰጧቸውም ወይም የማያውቁትን ነገር አልነገሯቸውም።

- **ማንነታቸውን በውል የማያውቋቸው ሶስት ሰዎች ለሚሽን መላካቸውን ይናገራሉ።**

ለሚሽን ተላኩ የተባሉት ሰዎች እነማን እንደሆኑ “ አዲስ አበባ ነዋሪ ነኝ የሚል...” በሚል በውል እንደማያውቁት በሚያመለክት መልክ ከመጥቀስ በሻገር ግለሰቦቹን አደጋ ውስጥ የሚጥል ምንም ነገር ሲናገሩ አልተደመጠም። ከዚህ በተጨማሪ አቶ አንዳርጋቸው ስለነዚህ ሶስት ሰዎች የተናገሩት ምን የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነው? የሚለውን ስናስብ ፦ ሊታየን የሚችለው፡ የወያኔ ደህንነቶች ስለ ሶስቱ ሰዎች ቀደም ብለው ካገኙት መረጃ በመነሳት ለአቶ የሰነዘሩላቸው ጥያቄ እንደሆነ ነው። ስለዚህ አቶ አንዳርጋቸው አሁንም ያረጋገጡላቸው እጃቸው ላይ ያለውን መረጃ እንጂ አዲስ መረጃ ሰጡ ማለት አይቻልም።

- **ብዙ ስራ ስሰራ የነበርኩት እኔ ነኝ። እኔን ተክቶ ሊሰራ ይችላል ብዬ የማስበው ሰው የለም ሲሉ ይደመጣሉ።**

የወያኔ ደህንነቶች አቶ አንዳርጋቸው እኔን ተክቶ በርሃ ገብቶ ሊሰራ የሚችል ሰው ማሰብ ያስቸግረኛል ማለታቸውን፤ እንደ ጅራፍ አጨኸው ድርጅቱ ማለትም ግንቦት ሰባት በሞት አፋፍ ላይ እንደሚገኝ አቶ አንዳርጋቸው ተናገሩ ብለው አቀረቡ። ይህ ደግሞ ሊያገኙት የቋመጡትን ነገር ባለማግኘታቸው የተፈጠረባቸውን ባዶነት በጩኸት ለመሸፈን መሞከራቸውን የሚያመለክት እንጂ አቶ አንዳርጋቸው ግንቦት7 የሚለውን ቃል እንኳ ሲናገሩ አልተደመጡም።

አቶ አንዳርጋቸው፤ የግንቦት ሰባት ቀጣይ እንቅስቃሴ ምን ይሆናል? ማን በኔ ምትክ ሊሰራ ይችላል? የሚለውን ጥያቄ ሊገምቱ እንጂ በትክክል ሊያውቁት አይችሉም። የተናገሩትም ግምታቸውን ነው። ግምታቸው ደግሞ እኔን የሚተካ ማንንም አይታየኝም የሚል ነው። ይህ ደግሞ ለድርጅቱ ቀጣይ እንቅስቃሴ ይጠቅም እንደሁ እንጂ ጉዳቱ አይታየኝም፡፡

- **በመጨረሻም እንዲህ ነው፤ እንዲህ ነው ብሎ ማለት አይገባም ሰዎች መጨነቅ የለባቸውም እኔ ደህና ነኝ ይሉና ከሆነ ሰው ጋር ተጨባብጠው ይለያያሉ።**

ይህ ነጥብ ወደ ቪዲዮው ቅንብር እንድንገባ ያደርገናል። ከላይ የሰፈረው አቶ አንዳርጋቸው ቃለ ምልልሱን ጨርሰው ከሆነ ሰው ጋር ተሰነባብተውና ተጨባብጠው ከመሄዳቸው በፊት የተናገሩት ነው። የተቀረጸውም በሁለተኛው ቃለ ምልልስ ወቅት መሆኑን ቀጥሎ ከማቀርባቸው ከቪዲዮ ክሊፖቹ ውስጥ ከወሰድኳቸው ፎቶዎች እንረዳለን።

በነገራችን ላይ ምን ያህሎቻችን አቶ አንዳርጋቸው ቢያንስ ሶስት ግዜ ቃለ ምልልስ ሲያደርጉ በቪዲዮ እንደተቀረጹ እንዳስተዋልን አላውቅም። እዎ! አቶ አንዳርጋቸው በሶስት የተለያየ ግዜ በቪዲዮ የተቀረጸ ቃለ ምልልስ(ምርመራ) አድርገዋል።

በቅርቡ የለቀቁት ለ8 ደቂቃ የሚዘልቀው ቪዲዮ የተቀናበረው ግን ከሁለተኛውና ከሶስተኛው ቃለ መጠይቅ ነው። ይህንንም በቀጣይ ከአለባበሳቸው መገንዘብ ይቻላል።




በሶስቱ ምስሎች ላይ ከሚታየው የአለባበሳቸው ልዩነት እንደምንረዳው አቶ አንዳርጋቸው ቢያንስ ቢያንስ ለ3 ግዜ ያህል ቪዲዮ እየተቀረጹ ለቃለ ምልልስ ወይም ለምርመራ ቀርበዋል።

በቅርቡ በፖሊስ ፕሮግራም የቀረበው የ 8 ደቂቃ ቪዲዮ የተቀናበረው ደግሞ ለሁለተኛና ለሶስተኛ ግዜ ሲቀርቡ በተቀረጹት ክሊፖች መሆኑን በቀጣይ እንመልከት።

በአንደኛውና በሁለተኛው ቀረጻ የለበሱት ቱታ አንድ ነው። ልዩነቱ በመጀመሪያው ላይ የለበሱት ቲሸርት ውሃ ሰማያዊ ሲሆን በሁለተኛው ቀረጻ ላይ ደግሞ ፒንክ መሰል ቲሸርት አድርገዋል። በሶስተኛ ቀረጻ ደግሞ ቱታው ከመጀመሪያው የተለየ ነው።




ከላይ ያለውን ምስል የወሰድኩት በቅርቡ ከተለቀቀው ክሊፕ 8.33 ሰከንድ ላይ ሲሆን ከታች የምታዩትን ደግሞ ከአንድ ሰከንድ በኋላ 8.34 ሰከንድ ላይ ያለው ምስል ነው፡፤ የልብሱን ልዩነት ልብ ይሏል።




እዚህ ጋ የሚነሳው ጥያቄ ለምን ይህን ማለትም ለሁለተኛ ግዜ የተቀረጸውን ቪዲዮ የመጨረሻ ፍሬሞች (ተሰናብተው ሲሄዱ የሚያሳየውን) በቅርቡ በለቀቀት ቪዲዮ መጨረሻ ላይ ማስገባት አስፈለገ? የሚለው ይመስለኛል።

ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሆናል ብለን የምንገምተው ለ3ኛ ግዜ በተቀረጸው ቪዲዮ ላይ በተፈጸመባቸው ድብደባ፤ ግርፊያና ስቃይ ሳቢያ ከተቀመጡበት መነሳት ባለመቻላቸው የግድ የስንብቱን ክፍል ከቀዳሚ ቪዲዮ ላይ ማስገባት ስላስፈለገ ነው የሚል ይሆናል።

ይህን ስንል ደግሞ ተቆርጦ የሚገባው ቪዲዮ እንዳያስታውቅ ለማድረግ ለምን መጀመሪያ የለበሱትን ቱታ በ3ኛው ቀረጻ ላይ እንዲለብሱ አልተደረገም የሚል ጥያቄ ያጭርብናል።

አሁንም ለዚህ ጥያቄ ሊሰጥ የሚችለው መልስ በቱታዎቹ ህብረ ቀለማት መመሳሰል ምክንያት የወያኔ ደህንነቶች አቶ አንዳርጋቸው ቱታ መቀየራቸውን አለማስተዋላቸው ነው። ለነገሩ ይህን የመሰለ የተረበሸ ኤዲቲግ የሰራ አካል ይህን ማስተዋል ባይችል አይገርምም።

በሁለተኛው ቃለ ምልልስ ወቅትም ቢሆን በቪዲዮው የመጨረሻ ፍሬሞች ላይ አቶ አንዳርጋቸው ከተቀመጡበት ተነስተው ከፊት ለፊታቸው ያለውን ሰው እስኪጨብጡ ድረስ ያለው እንቅስቃሴያቸው በሁለት ፍሬም ብቻ (ማለትም አንድ ማይክሮ ሰከንድ ብቻ) መውሰዱ በመሃሉ የተቆረጡ ፍሬሞች እንዳሉ የሚያመላክት ነው። አቶ አንዳርጋቸው ከተቀመጡበት ለመነሳት በሁለት እጃቸው ጠርጴዛውን ከተመረኮዙ በኋላ ቀጥሎ የሚታየው ፍሬም  ቆመው ሲጨባበጡ ነው።ይህ ደሞ ከተቀመጡበት ለመነሳት ስላልቻሉ ድጋፍ እንደተሰጣቸውና የተቆረጡትም ፍሬሞች የድጋፉን ክፍል የሚያሳዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ እንድገምት አድርጎኛል።

ለግንዛቤ ያህል በአንድ ማይክሮ ሰከን የሚከታተሉት ፍሬሞች ላይ ያለውን ግዙፍ የእንቅስቃሴ ርቀት ተመልከቱ




በሁለቱ ምስሎች መካከል በርካታ ፍሬሞች እንደተቆረጡ ግልጽ ነው። እነዚህ ፍሬሞች የተቆረጡት አንድም ምስላዊ ገበናን ለመደበቅ አልያም የማይፈለግ ድምጽን ለማውጣት ነው። የኔ ግምት ግን ወደ ምስሉ ያደላ ነው።

- **ከ 55-70 ሰከንድ ድረስ አለፍ አለፍ ብሎ  የስቃይ ደምጽ “ጩኸት” ይደመጣል**

በ 55ኛው ሰከንድ ላይ፤  1 ደቂቃ ከ 02 ሰከንድ ላይና በ 1 ደቂቃ 06 እስከ 1 ደቂቃ 09 ሰከንድ ድረስ ጎላ ባለ ድምጽ ከዚያ በኋላ ደግሞ ራቅ ባለ ድምጽ በጠቅላላው 4 ግዜ ያህል  የስቃይ ድምጽ ይሰማል። ይህ ድምጽ ተቃዋሚን ለማስበርገግና ምን ታመጣላችሁ አዎ! እናሰቃየዋለን! የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ሆን ብለው እንዳሰገቡት የሚገምቱ ወገኖች አሉ። ሌሎች ደግሞ የለም በስህተት እንጂ ይህን ያህል አዋራጅ ነገር ሆን ብለው ሊያደርጉ አይችሉም ይላሉ።

በስህተት ነው ለሚሉት ወገኖች፤ ስህተት ከሆነ ለምን ኤዲት ሲያደርጉ ጩኸቱን አላጠፉትም? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ለዚህ ጥያቄ መልስ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በችሎታም ይሁን ባለማስተዋል ማጥፋት አለመቻላቸው ብቻ ነው። በርግጥም በመጀመሪያና ሁለተኛ ላይ ያለውን ድምጽ ለማጥፋት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ድምጹ በሚሰማበት ሰከንድ አቶ አንዳርጋቸውም እየተናገሩ ስለነበር የሳቻውንም ቃል አብሮ ያጠፋልና ነው። ሶስተኛውና ጎላ ብሎ የሚሰማው ድምጽ ግን አቶ አንዳርጋቸው በማይናገሩበት ሰከንድ ስለነበር ያላጠፉት ለምን እንደሆነ ባይገባኝም ማጥፋት አስቸጋሪ አልነበረም።

በደምላላው ሲታይ ግን ቪዲዮውን ኤዲት ያደረገው አካል ማንም ይሁን ማን የሞተ ኤዲተር በመሆኑ የድምጹም ያለመጥፋት ከብቃት ማነስ ጋር ልናዳብለው እንችላለን። በበኩሌ አውቀው አደረጉት የሚለውን ሃሳብ ግን ለመቀበል ይቸግረኛል፤፡

- **የወያኔ ደህንነቶች ይህን በወጉም የልተሰለቀ ቪዲዮ በሚጮኸ ርዕስ አጅበው (በችኮላ ይመስላል) የለቀቁበት ምክንያት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ እንመልከት፡-**

የአቶ አንዳርጋቸውን ቪዲዮ በተመለከትኩበት ቅጽበት ወዲያውኑ በአይምሮዬ የመጣው፤ የወያኔ ደህንነቶች ይህን ቪዲዮ የለቀቁት *"ተላላኪው ማነው"* ለሚለው ለታማኝ በየነ አስረጂ ቃለ ምልልስ እንደ መልስ ምት አልያም እንደ ጉዳት ማባረጃ እንዲሆን አስበው ነው የሚል ነው ።

ይህን ግምቴን አጥብቄ እንድይዘው ያደረገኝ ደግሞ በወያኔ የፖሊስ ፕሮግራም የቀረበውን ዜና በድጋሚ ስሰማው ነው። ልብ ብላችሁ ከሆነ ዜናው የሚጀምረው "የኤርትራ መንግስት ተላላኪ በመሆን የሃገራችንን ሰላም ለማደፍረስ...." በማለት ነው። እናም ታማኝ በየነ *"ተላላኪው ማነው?"* በሚል መሪ - ርዕስ ዝግጅት እንደሚያቀርብ በኢሳት የተለቀቀውን ማስታወቂያ ሲያዩ ሳይቀድሙን እንቅደም አይነት እንዳዘጋጁት የነበረኝን ግምት አጠናክሮልኛል። በተጓዳኝም ተቃዋሚውን ተስፋ ለማስቆረጥና፤ በተቃዋሚው ቁጣ የተርበደበደውን የደጋፊያቸውን ሞራል ከፍ ለማድረግ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለቴ ነው።

**እንደ ማጠቃለያ**

አቶ አንዳርጋቸው በጠላት እጅ ከወደቁ አንድ ወር አለፋቸው። በዚህ ግዜ ውስጥ ግን የወያኔ ደህንነቶች ውሃ የሚቋጥር መረጃ እንዳላገኙ ከሚለቁት ቪዲዮ መረዳት አይከብድም። ይህ ደግሞ አቶ አንዳርጋቸው ምን ያህል ስቃይ እንዳሳለፉ እንድንገነዘብ ያደርገናል።

በበኩሌ አቶ አንዳርጋቸው ከዚህ በኋላ ምንም አሉ ምን...! ለጀግንነታቸው የምሰጠውን ክብር ቅንጣት ታክል አይቀንሰውም። ገርፈው በማይጠግቡት ገለው በማይረኩት ቂመኛ አረመኔዎች እጅ በእንዲህ አይነት የተረጋጋ መንፈስ ለአንድ ወር ቀርቶ ለአንድ ቀን መዝለቅ ጀግንነት ነው።

ጠላትም ቢሆን ከምርኮኛው ላይ የሚያገኘውን መረጃ ሊጠቀምበት የሚችለው መረጃው ማፈትለኩ እስካልታወቀ ድረስ በመሆኑ አቶ አንዳርጋቸው ከዚህ በኋላ ለወያኔ መንግስት የሚሰጡት ምንም አይነት መረጃ ድርጅቱን ሊጎዳው ይችላል ብዬ አልገምትም። እሳቸው በስቃይ ያሳለፉት አንድ ወር ድርጅቱ የራሱን ጥንቃቄ እንዲያደርግና ያፈተለኩ መረጃዎች እንኳ ቢኖሩ ጉዳት ሳያደርሱ የሚመክኑበትን እቅድ ለመንደፍ ሰፊ ግዜ የሰጠ ነውና፡፤ለዚህም ክብር ለአቶ አንዳርጋቸው ይሁን እላለሁ!!

ስለሆነም ከዚህ በኋላ አቶ አንዳርጋቸው ወደፊት ስለሚናገሩት ወይም ሊናገሩ ስለሚችሉት ነገር በመገመት፤ በማሰብም ሆነ በመፍራት የሚጠፋ ግዜ መኖር ያለበት አይመስለኝም። ከዚህ በኋላ ወያኔ የፈለገቺውን ፕሮፓጋንዳ ሰርታ አቶ አንዳርጋቸውን ይዛ ብቅ ብትል በተቃዋሚው ጎራ ምንም አይነት የሞራል ስብራት ልታደርስ አትችልም።

አቶ አንዳርጋቸው ከማንም በላይ ኃላፊነታቸውን ታሪክ ሲዘከረው በሚኖር ብቃትና ጀግንነት ተወጥተዋል።

ቀሪው ኃላፊነት የኛ ነው።ያለንን ግዜ ፤አቅምና ችሎታ ተጠቅመን ጀግናችንን መታደግ!!! በተጓዳኝም የአቶ አንዳርጋቸውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እጅ ለእጅ ተያይዘን መነሳት ይገባናል።

ቆርጦ ቀጥሎቹ የወይኔ ፕሮፓጋንዲስቶች በአግባቡ ቆርጠው መቀጠልም ተስኗቸው እየተደናበሩ ናቸው። ፕሮፓጋንዳቸው መልሶ እራሳቸውን እየበላቸው ነው። ከኛ የሚጠበቅብን ከመቼውም ግዜ መረርና ጠንከር ያለ እንቅስቃሴ ማድረግ ብቻ ነው። በአካባቢያችን ያሉ የወያኔ ደጋፊዎችን ስንመለከት ወያኔ በአንዳርጋቸው ላይ እየተፈጸመ ያለውን ግፍ እናስብ! እናም ማድረግ ያለብንን እናድርግ።

የኢትዮጵያ ትንሣኤ ቅርብ ነው!

ሳምሶን አስፋው
ቋጠሮ ገጽ